# የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ እና 370 መሠረት የወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ታህሣስ 17 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ኤልጌል ሆቴል ይካሄዳል:: በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን የማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል::

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

የማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡- ኦሮሚያ ክልል፣ ሸገር ከተማ፣ ፉሪ ክ/ከተማ

ስ.ቁ. 011-338-433 ድረ-ገጽ http://www.wasasamfi.com

የኢብባ ፈቃድ ቁጥር፡- MFI/017/2000 የተከፈለ ዋና ገንዘብ ብር፡- 10,000,000.00

## 2. የ29ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1. የጉባዔውን ድምጽ ቆጣሪዎችን እና ጸሐፊ መሰየም
2.2. የእለቱን አጀንዳዎች ተወያይቶ ማጽደቅ
2.3. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የዳይሬክተሮች ቦርድን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ
2.4. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የውጭ አዲተርን ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ
2.5. በተ.ቁ. 2.3 እና 2.4 የቀረቡ ሪፖርቶችን ተወያይቶ ማጽደቅ
2.6. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የተጣራ ትርፍ ድርሻ ላይ የቀረበውን ውሳኔ ሃሳብ ተወያይቶ ማጽደቅ
2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ የሥራ ዋጋን መወሰን
2.8. የጉባዔውን ቃለ-ጉባዔ ማጽደቅ

## 3. ማሳሰቢያ

3.1. በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ ቁጥር 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀናት በፊት ሰበታ አለምገና በሚገኘው ዋናው መ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆን እና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን::

3.2. የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውን እና ኮፒውን በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ:: እንዲሁም ትውለደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ(ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን::

**የወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ**

WASASA MICROFINANCE S.C.

CamScanner